የተከበራችሁ በሚኒሶታ አካባቢ ያላችሁ ካህናት አባቶቻችን

ከቀሲስ አስተርአየ

ኅዳር 7 ቀን 2018 ዓ/ም

አስተማሪ በሆነ ተግሳጽ አቋማችሁን የገለጻችሁ የመኑሴታ ካህናት አባቶቻችን ሆይ! ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ብጹዐን ናችሁ ! ትላችኋለች።

አባቶች ሆይ! እንደምታውቁት ይህን አረፍተ ነገረ የወሰድኩት "ያእምር ኩሉ ለለአሐዱ ምቋመዚአሁ ወይፈጽም ግብሮ በተግሣጽ። ወይኩኑ ኩሎሙ በአሐዱ ሕሊና ወበአሐዱ መንፈስ (አ 9 294)። ከሚለው ከቤተ ክርስቲያናችን መርሆ ነው። እናንተ ያሳያችሁትን አቋም ደፍሮ የቤተ ክርስቲያናችንብ ክህነታዊ አቋም የገለጸ የለም። ይልቁንም ጦርነት በተነሳበት አገር ወታደር እየተከተለ fast food እና የጦር መሳሪያ በመቸብቸብ ትርፍ እንጅ ስለ ተገዳዩና ገዳዩ ከማይስቡ ነጋዴወች የባሱ አስመሳይ ጳጳሳት ቆሞሳትና ሰባክያን ስማቸውን በተደራረበ የማዕርጋት ስሞቻቸውን አጅበው በህዝቡ ወቅታዊ ችግር አዛኝ መስለው የግል ጥቅማቸውን ከሚያጋብሱ አስመሳዮች እጅግ ተሸላችሁ ለተልእኳችሁ በመቆም ድምጽ በማሰማታችሁ እንኳን ለህሊናችሁ እርካታ በቃችሁ። ሲኖዶሱ ሊያደርገው የሚገባውን ሃላፊነት በመጠቆም አቋማችሁን ያሳያችሁትበት መግለጫ የሚደነቅ ነው። ይሁን እንጅ ጌታችን ከርስቶስ "ዘአዝለፈ ትእግሥቶ ውእቱ ይድኅን " እንዳለው ጀምሮ በመተው የጸደቀ የለም።

ይልቁንም መጽሐፈ ቀኖናችን "ወምግባረ ካህናት ሠናይት ትበቁዖሙ ለብዙኃን እስመ ውእቱ ይትሜሰሉ ባቲ ወከማሁ ካዕበ ኃጢአቶሙኒ ትፌስዮሙ ለሰብእ ሀካያነ እምሠናያት"(አን 9 297)። እንዳልው እናንተ ዛሬ ያሳለፋችሁትን ውሳኔ ለተጉት ካህናት ምሳሌነቱ ይጠቅማል። እጅግ ርቀው ርህራሄ የራቃቸውን ነጋዴወች ከባሱ ስግብግብ ካህናት ወደ ቀልባቸው እንዲመለሱ ይረዳቸው ይሆናል ብየ እገምታለሁ።

አሁን ያሉት ሰወች "ማንም ራሱን አያታል ከእናንተ ማንም በዚች ዓለም ጥበበኛ የሆነ ቢመስለው ጥበበኛ ይሆን ዘንድ ሞኝ ይሁን። የዚች ዓለም ጥበብ በግዚአ ብሔር ፊት ሞኝነት ነውና"(1 ቆሮ 3፡18) የሚለውን ረስተው በንዝህላልነት የፈጸሙትን የቀደመ በደላቸውን ለመሸፈን ለነሱ ጥበብ በመሰላቸው ሞኝነት ከነሱ ይልቅ በጥበብ የቀደማቸውን ሕዝብ ለመደለል በሚያደርጉት ሙከራ ሲዋረዱ እየታዩ ነው። ብዙወች የሲኖዶስ አባላት በዘር በቋንቋና በሃይማኖት ተከፋፍሎ ሕዝቡን እርስ በርሱ ከሚያጋድሉ ተገለባባጮች ጋራ በመሰለፍ በየራሳቸው ኃጢአት ተጠቅልለው፡ ባዶ ቃል እያሰሙ ህዝብ ክራስቲያኑን ከማስፈጀት በቀር ቤተ ክርስቲያን የዘር ማጥፋቱ ክስ ይዛ ለዓለም እንዳትወጣ ቤተ ክርስቲያናችንን እያፈረችባቸው ነው። ለዘመናት ዘበኞች ሆነው ኢትዮጵያን ከጠላት ሲጠበቋት በኖሩ አርቶዶክሳውያን ልጆች አጥንት ሥጋና ደም የኢትዮጵያ ገጸምድር ተሸፍኖ ባለበት ወቅት የጀመራችሁትን የሰቆቃውና የዋይታ ድምጽ እንዳታቋርጡ "ግንብ ለመሥራት አቅዶ ለመደምደም ቢያቅተው ተጀምሮ የቀረውን ያዩ ሁሉ ይሳለቁበታል"(ሉቃ ም 14፡ ቁ 28_30)። በሚለው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ማስጠንቀቂያ ላሳስባችሁ እወዳለሁ። ቅዱስ አትናቴወስ "ጽኑዓን ይደክሙ እስመ አኃለቁ ሥጋሆሙ በዝሙት (ቅ አ ቁ 82)" እንዳለውም ሲኖዶሱ በዝሙትና በመሳሰሉት አሳፋሪ ተግባራትና አቋም በመቀያየር የሞተ ስለሆነ ያቀረባችሁትን ጥሪ ተቀብሎ በተግባር ያውለዋል በሚል ተስፋ አትታለሉ። "ኃያላን ይጸብሱ እስመ ሰፍሑ እደዊሆሙ ውስተ ትዕግልት ወአብከዩ እቤረ ወዕጓለ ማውታ(83) እንዳለውም፡- የሻሸመኔን ሕዝበ ክርስቲያን ጥቁር አስለብሰው ካሰፈጁ በኋላ እራሳቸውን የደበቁ ናቸው።

የጀመራችሁት ድምጽ "እስመ በስመ ሰለስቱ ስም ይቀውም ኩሉ ነገር" እንደተባለው ከዚህ በታች ከአንድ እስከ ሶስት በተገለጹ ጥቅሶች ላይ የተመሥረተ ነውና የሴረኞች ጫጫታ ሊያፍነው የማይችል በኦሪቱ (ዘዳ 19፡15)፡ በክርስቶስ (ማቴ 18፡16)። በሐዋርያትም (2ኛ ቆሮ 13፡1) ትምህርት በጽኑ መሠረት የተደግፈ ነውና በጀመራችሁት አቋም ጸንታችሁ ቁሙ!

1ኛ፡-ያንድ የአቤል ደም በሰው ላይ ያስከተለው የተፈጥሮ ክስ (ዘፍ 4፡11)

2ኛ፡-ሰበነክ የሆነውን ዘር በመሬት በመድፋቱ ያስከተለው የሞት ፍርድ (ዘፍ 38፡10)

3ኛ፡- ከ40 ቀን የሰውነት ቅርጹ ከተሟላለት በኋል ያስወረደ ሰው እንደገደለ (ቅ አ ቁ 113)

ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያናችን ከዚህ በላይ በተገለጹት መመሪያውቿ የምታወግዘውና በሰማይና በምድር ልትከሰው ግዴታ ያለባት የዘርጥፋት በሕዝብ ክርስቲያኑ ላይ እስከዚህች ቅጽበት እየተካሄደ ነው። ሲኖዶሱ በነዚህ መስፈርቶች የተሟላውን የዘር ማጥራት ግድያ በትረ መግሥቱን እየተፈራረቁ የሚናጠቁት ሰወች በሕዝቤ ላይ እየፈጸሙ ናቸውና እፋረዳለሁ ብላ እንዳትነሳ ታፍናለች። የሚካሄደውን የዘር ጥፋት በቤተ ክርስቲያናችን አስተምሕሮ ለመግለጽ አቅም የሌላቸው ወይም እይተረዱ ሆን ብለው ደካማና አሳሳች በሆነ አቀራረባቸው ዩቱብ ክፍተው በሚያስተጋቡት ጫጫታ የተያዘውን ዓቢይ ጉዳይና ተገቢውን ድምጽ እየሸፈኑት ናቸው። የመንግሥት አንደበት ሆነው ሌትና ቀን ጎሮጉቸው እስኪሰነጠቅ የሚለፈልፉትም የሚጨፈጨፈውን ሕዝብ እንደ ጠላት በመመልከት ድምጹ እንዳይሰማ እያፈኑት ናቸው። ይልቁንም መንግሥት ለግድቡና ለወደቡ ማሰመለስ የሚደረገውን ጥረት ደጋፊ ለማሳጣት የሚደረግ ሴራ እንደሆነ ደጋግመው ሲናገሩ እየተሰሙ ናቸው።

እናንተ የመኒሶታ አባቶች ያሰማችሁት ድምጽ "ጌታ እስኪመጣ ይዘገያል ብሎ በልቡ እያሰበ ባልንጀሮቹን ሊመታ ቢጀምር ከሰካሮችም ጋራ እየበላና እየጠጣ ሳለ ጌታው ባልጠበቃት ቀንና ባላወቃት ሰአት ሰዓት ይመጣል ከሁለት ይሰነጥቀዋል፡፡እድሉንም ከግብዞች ጋራ ያደርግበታል። በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል።(ማቴ 24፡48_51) የሚለው የክርስቶስ ቃል በሲኖዶሱ ላይ ያነጣጠረ ጦር አድርጎታል። በሲኖዶሱ ውስጥ ያሉት አቅጣጫ እየቀያየሩ ህዝቡን ከሚያጋድሉት ፖለቲከኝሎች ጋራ እየበሉና እየጠጡ ከሁለት በላይ በብዙ ቁጥር ተከፋፍለው እየደበደቡና አያስደባደቡ ናቸው። ከተሸከሙት በደልና ኃአጢአት ክብደት የተነሳ የገዛ ሕሊናቸው እርስ በርሱ በመካሰስ ፍጭት የሚገፋው ጥርሳቸውም እየተፋጨ ነው።

ሕዝበ ክርስቲያኑንም ከፋልፍለው እርስ በርሱ እያፋጨት ነው። እናንተ ግን “ፈትኖ መልካም የሆነውን የሚያደርግ ከራሱ ህሊናዊ ክስ ነጻ በመሆኑ ብጹዕ ነው”(ሮሜ 14፡22) እንዳለው ሕዝበ ክርስቲያኑ ያለበትንና የሲኖዶሱን ግዴለሽነት አጥንታችሁ አውርዳችሁ አውጥታችሁ ራሳችሁን ፈትናችሁ መልካም መስሎ የታያችሁን **ይህን ውሳኔ በመወሰናችሁ** ብጹዓን ናችሁ።